# የአቶ ኢሳያስ "ሁሉም ነገር የለም" ቃለ-ምልልስ

**መስፍን ታሪኩ**

tmesfin20@gmail.com

ከጊዜ ወደ ጊዜ መልካቸውና ዊም አቀራረጣቸው ብሎም አገዛዛቸው ከናዚው አዶልፍ ሂትለር ጋር እየተመሳሰሉ የመጡት ጎረቤታችን የአስመራው ፕሬዚዳንት አቶ ኢሳያስ አፈወርቂ፤ ከአራት ጋዜጠኞች ፊት ለፊት እንደ ተጠያቂ ሳይሆን እንደ ዳኛ ቁጭ ብለዋል—ብይን የሚሰጡ ይመስል። እንዲያውም ጋዜጠኞቹን 'ምንም ነገር በሌለበት ሁኔታ ምን ልትሰሩ መጣችሁ?፣ አሁን ህዝቡ ላይ ስለምሎሁበት ተዘጋጁ!' የሚሉ ይመስላሉ።...እንደ እውነቱ ከሆነ ሁለት ሰዓት ገደማ በፈጀው የመጀመሪያው ክፍል ቃለ-ምልልሳቸው ላይ ሰውዬው ፈገግ ሲሉ አላየኋቸውም። ፈገግታቸውን የትኛው የአስመራ ሰላቢ እንደ ወሰደባቸው አይታወቅም። ፊታቸውን ክስክስ አድርገው ጋዜጠኞቻቸውን ይቃኛሉ።...እናንተዬ ለካስ ፈገግታም እንደ ጉም እንዲህ በንኖ ደብዛው ይጠፋልና?!...መቼም "የአበራሽን ጠባሳ ያየ በእሳት አይጫወትም" እንደሚባለው፤ የአቶ ኢሳያስን ተስፋ ቆራጭ ፊት ቴሌቪዥን ውስጥ ያየ የሻዕቢያ ሹምም ከእንግዲህ ፈገግታን እንደ ቀልድ ቆጥሯት የሚጫወትባት አይመስለኝም—እርሷም ብትሆን ኤርትራ ውስጥ ዋጋዋ ውድ ነውና ።

ያም ሆነ ይህ ግን የ'ወዲ አፎም'ን ቃለ-ምልልስ አዳምጬ ሳበቃ፤ እጅግ በመገረም "ታዲያ ኤርትራ ውስጥ ያለው ነገር ምንድነው?፣ ሁሉም ነገር ከሌለስ ሀገሪቱ ውስጥ ያሉት ሰውዬው ብቻ ናቸው እንዴ?" ስል ራሴን ጠየቅኩ። እውነትም ከረጅም ጊዜ ቆይታ በኋላ በሀገራቸው የመገናኛ ብዙሃን አማካኝነት ብቅ ብለው በሰጡት ቃለ-መጠይቅ ላይ ሁሉንም ነገር በ"የለም" ጀምረው በ"የለም" የጨረሱት የአስመራው የሽብር ቡድን መሪ፤ ከጋዜጠኞቹ ጋር ያደረጉት አሰልቺ ቆይታ እኔን በአያሌው አስደምሞኛል። 'ምን ማለት ነው ሁሉም ነገር የለም ማለት?፣ በ'የለም' ምላሽ የታጀበው የሰውዬው ቃለ-ምልልስ ሲጠቃለል ምን ማለትስ ይሆን?...ወዘተ.' የሚሉ ጥያቄዎችም እየተደጋገሙ በውስጤ ተመላለሱ።...

...ግና ነገሩ "ሳይደግስ አይጣላም" እንዲሉት ዓይነት ሆኖ ነው መሰል፤ አይጋ ፎረም የተሰኘው ድረ-ገፅ ኤዲተሮች በጉዳዩ ዙሪያ ዕውቀት ጠገብ የሆነውን ውሰጥ አዋቂ ወዳጃቸውን በመጠየቅ የቃለ-ምልልሱን ጥቅል ጭብጥ በካርቱን በታጀበ ግሩም ምልከታ አማካኝነት በመግለፅ በውስጤ ለሚመላለሱት ጥያቄዎች ምላሽ ሰጥተዋል።...አዎ! ከኤዲተሮቹ ወዳጅ የተገኘው የትግርኛ ምላሽ እንዲህ የሚነበብ ነው።...

..."ዶላር የለን፣ አፍኩም ዕጸው፤

ባኒ የለን፣ ጋባ ኣራርዩ፤

ከኒና የለን፣ ናብ ደብተራ ኪዱ፤

ሳሙና የለን፣ ሽብጢ ተጠቐሙ፤

መብርሒቲ የለን፣ ብእዋኑ ደቅሱ፤

መጉዓዝያ የለን፣ መጸዓኛ ዓድጉ፤

የለን…የለን…ፈጺሙ የለን እንተበልና፤

የለን የለን አይትዘምሩ፤

ካርሼሊ ከይትሓድሩ።”… ታዲያ ይህ የአቶ ኢሳያስን “የሁሉም ነገር የለም” ቃለ-ምልልስን በትክክለኛ ማጠቃለያነት የሚወክለው አጭርና ጣፋጭ ምልከታ በቁም ትርጉሙ ወደ አማርኛ ሲመለስ፦

“ዶላር የለም፣ አፋችሁን ዝጉ፤

ዳቦ የለም፣ የጋባ ፍሬን ብሉ፤

መድሃኒት የለም፣ ወደ ደብተራ ጋ ሂዱ፤

ሳሙና የለም፣ እንዶድ ተጠቀሙ፤

መብራት የለም፣ በጊዜ ተኙ፤

መጓጓዣ የለም፣ መጫኛ ግዙ፤

የለም…የለም…ሁሌም የለም ስንላችሁ፤

አትዘምሩ የለም የለም እያላችሁ፤

ከርቸሌ እንዳይሆን ማደሪያችሁ።” የማለት ያህል ነው። ታዲያ እኔም ከቃለ-ምልልሱ በመነሳት ጥቂት መሰል ዕውነታዎችን ልጨምር ወደድኩ።….

“ማይ የለን፣ ናብ ቐይሕ ባሕሪ ኪዱ፤

ነዳዲ የለን፣ ካሮሳ ተጠቐሙ፤

ጣፍ የለን፣ ናብ ኢትዮጵያ ኪዱ፤

ስጋ የለን፣ ዓደስ ብልኡ፤

ዕብየት የለን፣ ንሲንጋፖር ራዕዩ።"...የአማርኛ ቀጥተኛ ትርጉማቸውም፦

"ውሃ የለም፣ ወደ ቀይ ባህር ሂዱ፤

ነዳጅ የለም፣ የአህያ ጋሪ ተጠቀሙ፤

ጤፍ የለም፣ ወደ ኢትዮጵያ ሂዱ፤

ስጋ የለም፣ የምስር ሽሮ ብሉ፤

ዕድገት የለም፣ ሲንጋፖርን እዩ።" የማለት ያህል ነው።

እርግጥም የአስመራው ቁንጮ በቃለ-ምልልሳቸው ላይ በዚያች ትንሽዬ ሀገር ውስጥ፤ የምግብ ሰብል፣ የንፁህ ውሃ አቅርቦት፣ የየብስና የአየር መጓጓዣዎች እንዲሁም ወደቦችና የአየር ማረፊያዎች አለመኖራቸውን ለህዝቡ የማስጠንቀቅ ያህል ፊታቸውን ኮሶ አስመስለው ራሳቸው በአንደበታቸው መናገራቸው፤ ቀደም ሲል የቀረበውን ጣፋጭ ምልከታ ትክክለኛነት የሚያረጋግጥ ነው። ይሁንና እዚህ ላይ ሃቁን ይበልጥ ለመረዳት በእነ የሻዕቢያው ቱልቱላ ነፊ ጋዜጠኛ ሱሌይማን ዑስማን አማካኝነት ለአቶ ኢሳያስ የቀረቡት ጥያቄዎችንና ምላሾቻቸውን በጥቂቱ ዳሰሰን መመልከት የሚያስፈልግ ይመስለኛል። በአሁኑ ወቅት (ለዚያውም ጋዜጠኞቹ ራሳቸው ኤርትራ የማታከብረውንና 'የሃበሻ አዲስ ዓመት በዓልን እንዲሁም ከክረምት ወደ በጋ መሸጋገርን አስመልክቶ' የሚል የውሸት ታፔላ በለጠፉለት ቃለ-መጠይቅ) እነዚህን ጥያቄዎች መመለስ ለአቶ ኢሳያስ ያስፈለገበትን አስገዳጅ ሁኔታን መቃኘትም እንዲሁ።...

በምግብ ሰብል ራስን የመቻል ጉዳይን እንደ አንድ የኤክስቴንሽን ባለሙያ ከመዘርዘር አልፈው በምስራቅ አፍሪካ በየጊዜው የሚከሰተው የድርቅ አደጋ እንደ እርሳቸው ዓይነት ባሉ ሀገራት ውስጥ በዝናብ እጥረት ብቻ የሚፈጠር የሚመስላቸው ሰውዬው፤ የህዝቡን ችግር በማድበስበስ "አስመራ ውስጥ ብቻ አልዘነበም እንጂ በሌሎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ጥሩ ነበር። ለማንኛውም ክረምቱ ሲወጣ የምናውቀው ጉዳይ ይሆናል" ብለዋል። ግና ኤርትራ ውስጥ በተለያዩ ጊዜያት የሚከሰተው ድርቅ ከዝናብ ባሻገር አቶ ኢሳያስ የሚከተሉት የኢኮኖሚ ፖሊሲ ፍልስፍናም ዋነኛው ምክንያት ነው። እንዲያውም የችግሩ ማጠንጠኛ ይኸው የወዲ አፎም ፖሊሲ ነው ቢባል ከዕውነታው ብዙም መራቅ አይሆንም። ታዲያ ይህ ፖለሲ ሌላው ቀርቶ ህዝቡ ለኑሮ የሚያስፈልጉትን መሰረታዊ ጉዳዮች ማለትም ምግብ፣ ውሃ፣ ዘይት፣ ስኳር፣ መጓጓዣ፣ የመፃፍና

የመናገር ነፃነት…ወዘተ. ማሟላት ያልቻለ በመሆኑ በአሁኑ ወቅት እነዚህን ጉዳዮች የአቶ ኢሳያስ ጋዜጠኞች እንዲያነሷቸው ተደርጎ፤ ህዝቡ አፉን እንዲዘጋ ለማድረግ ሰውዬው ባልተለመደ ሁኔታ እርሳቸውና ጋዜጠኞቻቸው ‘የሐበሻ አዲስ ዓመት’ በሚሉት ወቅት ቃለ-ምልልስ ለማድረግ ተገደዋል።

የአቶ ኢሳያስ የራስን የተፈጥሮ ፀጋ አሟጦ ተጠቅሞ ከማደግ ይልቅ በሌሎች አንጡራ ሀብት ላይ ተንጠላጥሎ በጦረኝነት አባዜ የመበልፀግ አስገራሚ የኢኮኖሚ ፍልስፍና የሀገሪቱን ምጣኔ ሀብት ላለፉት 22 ዓመታት ከድጡ ወደ ማጡ ከትቶታል። እርግጥ የኤርትራ ህዝብ ከዛሬ ሁለት አስርት ዓመታት በፊት በአስመራው ቡድን ሀገሩ ሲንጋፖርንና ታይዋንን እንደምትሆን የተስፋ ዳቦ ተሰጥቶት የነበረ እንደመሆኑ መጠን፤ ዛሬ ላይ ሌላው ቀርቶ ቀደም ሲል የጠቀስኳቸውን መሰረታዊ ፍላጎቱን መጠየቁ አግባብነት አለው። ምክንያቱም የሀገሩ ምጣኔ ሀብት በእነዚህ ዓመታት ውስጥ አድሮ ቃሪያ እንዲሉት ዓይነት ሰርክ ከማሽቆልቆል በስተቀር አንድም ስንዝር ፊት ሲል ባለማየቱ ነው።

በዚህም ምክንያት በአሁኑ ወቅት በህዝቡና በሻዕቢያው ቡድን መካከል ቅራኔ ተፈጥሯል፡፡ ለቅራኔው መነሻም የተለያዩ ምክንያቶች ይጠቀሳሉ፡፡ የአሥመራው ቡድን ከሁሉም ጎረቤት ሀገሮች ጋር የነበረው ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት መቋረጡ፣ ኢኮኖሚው የሠራተኛ ጉልበት ማጣቱ እና በዋነኛነት ከውጭ በሚላክ ድጎማ ላይ መመስረቱ ከሚጠቀሱት በርካታ ምክንያቶች ውስጥ ጥቂቶቹ ናቸው፡፡

ፍላጐቱን በአካባቢው ሀገራት ላይ በኃይል ለመጫን የሚፈልገውና ወታደራዊ ጀብደኝነትን እንደ “መጨረሻ ካርድ” የሚመለከተው የሻዕቢያው ቡድን፤ ከሁሉም ጎረቤቶቹ ጋር በፈጠረው ግጭት ሳቢያ ከጋራ ጥቅም አንጻር ማግኘት ይገባው የነበረው ኢኮኖሚያዊ ትሩፋት ተቋርጧል፡፡ በተለይም ከኢትዮጵያ ጋር የነበረው ግንኙነት መቋረጡ ለኢኮኖሚው ማሽቆልቆል ተጠቃሽ ነው፡፡

ሻዕቢያ “እመራዋለሁ” ለሚለው ኢኮኖሚ መድቀቅ በምክንያትነት የሚቆጠረው ሌላው ጉዳይ የሠራተኛ ጉልበት እጥረት ነው፡፡ ይኸውም በሀገሪቱ አምራች ዜጋ የሚባለው ወጣቱ ኃይል እየታፈሰ ሠራዊቱ ውስጥ ገብቶ መፈናፈኛ ማጣቱና ከክፍያ ነፃ ለሆነ የጉልበት ብዝበዛ መጋለጡ ኢኮኖሚው የሰራተኛ ጉልበት እጥረት እንዲገጥመው አድርጓል፡፡ እናም አርሶ አደሮች ባጋጠማቸው የሠራተኛ እጥረት ምክንያት ምርታቸውን በአግባቡ ሊሰበስቡ አልቻሉም፡፡

ሌላው ለሻዕቢያ ኢኮኖሚ መድቀቅ ተጠቃሽ ምክንያት የሀገሪቱ ኢኮኖሚ ሲሶው ያህል በሀገር ውስጥ ከሚገኝ ገቢ ይልቅ ውጭ ያሉ ዜጎች ከሚያዋጡት ገንዘብ የሚደጎም መሆኑ ነው፡፡ ሆኖም በውጭ ጥሮ ግሮ የተለያዩ ሥራዎችን እያከናወነ የገንዘብ ድጎማ ያደርግ የነበረው

ኤርትራዊ ባለፋት ዓመታት የኤርትራን መንግሥት የኪራይ ሰብሳቢነት አባዜ በመረዳቱ ይልክ የነበረውን ገንዘብ ቀንሷል፡፡ በቅርቡ ደግሞ በመንግሥታቱ ድርጅት አማካኝነት በተጣለበት የማዕቀብ ቅጣት ሳቢያ አንዳንድ ሀገራት የኤርትራ ቆንስላዎች ሀገራቸው ውስጥ ከሚገኙ ኤርትራዊያን የሁለት በመቶ የግዳጅ ቀረጥ እንዳይሰበስቡ በማገዳቸው የአቶ ኢሳያስ የኪራይ መሰብሰቢያ አቁማዳዎች እየደረቁ ናቸው፡፡ እናም ከዝናብ በባሰ ሁኔታ የኤርትራ ህዝብ ዛሬም ድረስ በምግብ ሰብል ራሱን ያልቻለበት ምክንያት ወዲ አፎም የሚከተሉት የተሳሳተ የጠረኝነት ፖሊሲ ዋነኛው መሆኑን መገንዘብ የሚገባ ይመስለኛል።

እስቲ የኢኮኖሚውን ጉዳይእዚህ ላይ ገታ ላድርገውና ወደ ሌላኛው የቃለ-መጠይቁ ደርዝ ልውሰዳችሁ። ራሳቸው በመረጧቸው ጋዜጠኞች በተሰናዳው፣ ድግግሞሽ በበዛበት፣ መያዣና መጨበጫ በሌለው እንዲሁም በማደናገሪያ መልሶች በተሞላው የአቶ ኢሳያስ ማስፈራሪያ ቃለ-ምልልስ ላይ ፣ "በአስመራና በአካባቢዋ እንዲሁም በሀገሪቱ ገጠሮችና ከተማዎች የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ችግር አለ። ይህንን ለመፍታት ምን እንደታሰበ ብታብራሩልን?" ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ "መልስ ያልሆነ" አስቂኝ መልስ ለመስጠት ሞክረዋል፡፡ ቀልጠፍ ብለውም እንዲህ አሉ።..."አንድ ነገር በግልፅ መነጋገር አለብን። እርሱም ሰው ነው እንጂ ወደ ውሃ የሚሄደው፣ ውሃ ወደ ሰው አይመጣም።"...እናንተዬ እንዴት ነው ነገሩ?!...የአቶ ኢሳያስ ንፁህ የመጠጥ ውሃን የማዳረስ ፖሊሲ ሁሉንም የሀገሪቱን ህዝብ ውሃ ወዳለበት ቦታ መውሰድ ነው እንዴ? እንግዲህስ ከሆነ ህዝቡ የሚሄደው የት ነው? ቀይ ባህር ወይስ የት?... እግረ መንገዳቸውንም ለመረጋጋት ይረዳ ዘንድ ለምሳሌ የአስመራና የመንደፈራ ከተማ ህዝቦች በየትኛው የቀይ ባህር አቅጣጫ እንደተመደቡ ቢነግሩን ጥሩ ነው— ማን በምስራቅና ማን በምዕራብ እንዲሁም የትኛው ህዝብ በባህሩ ሰሜንና ደቡብ ክፍል ተመድቦ እንደሆነ?...እኔ የምለው ቀይ ባህር ላይ የሚገኘው የምፅዋ ህዝብስ ጉርጉሱም ላይ ነው የሚሰፍረው ወይስ ቦታ ቀይሮ ሌላ ቦታ ይሄዳል?...ቂ.ቂ.ቂ...መቼም የአቶ ኢሳያስ 'በሰው ቁስል እንጨት ስደድበት' ትንተና ሌላም የሚያናግር ነው፡፡...

...እኔን ግርም ያለኝ ሌላው ጉዳይ አቶ ኢሳያስ ከ22 ዓመት በፊት እርሷን እንሆናለን ያሏትን ሲንጋፖርን ዛሬም በሽማግሌ ጭንቅላታቸው ለመርሳት አለመሞከራቸው ነው። ምንም እንኳን ለአስመራው ቡድን መሪ ስለ ሲንጋፖር ዛሬ ላይ ማውራት ሃፍረትን የሚያጭር ቢሆንም፤ 'ኢሱ' ግን ምንም አልገደዳቸውም። ህሊና ካለው ሰው አተያይ ወጣ ብለው የሲንጋፖርን አንድ ትልቅ ከተማ በመጥቀስ 'እርሷ እንኳን ውሃ የላትም' በማለት ለማደናገሪያነት ያቺን የዕድገት ተምሳሌት ሀገር ሊጠቀሙባት ሞክረዋል። ነገርዬው በገደምዳሜው ሲታይ 'እንኳንስ እኛ ቀርቶ ሲንጋፖርን የሚያክል የዕድገት ተጠቃሽ ሀገር ከተማም ውሃ የላትም' በማለት ህዝቡን አርፈህ ተቀመጥ በማለት ጥያቄውን ለማዳፈን የተዘየደ ማስፈራሪያ መሆኑ ከማንም የተሰወረ ጉዳይ

አይደለም። ዳሩ ግን መሰረታዊ የህዝብ ጥያቄን እያስፈራሩ በማደናገር እስከ መቼ ድረስ መዝለቅ እንደሚቻል የሚያውቁት አቶ ኢሳያስ ብቻ ናቸው።…እኔ ግን ውሃ የጠማው ህዝብ ጥማቱ ጊዜ የሚሰጠው አይመስለኝም– በየውሃ ማደያው ቦታ ጀሪካኑን እንደ ባቡር ቀጣጥሎ በመደርደር እየጠበቀ እምባውን ሊጠጣ አይችልምና። እናም ውሃ የጠማው ህዝብ ሁኔታው ሲብስ የሻዕቢያን ሹማምንቶች መቅኒ እያወጣ ከመጠጣት ወደ ኋላ የሚል አይመስለኝም።

አቶ ኢሳያስ የሀገራቸው ህዝባዊ ጥያቄዎች ዕለት ወደ ዕለት እየባሱ ሲሄዱ ያገኙት አዲስ ዘዴ ችግሩን መልሶ በህዝቡ ላይ ማላከክ ይመስላል። ሰውዬው በአንድ በኩል ውሃ የለም እያሉ በሌላ በኩል ደግሞ ህዝቡ ውሃን አብቃቅቶ መጠቀም እንዳለበት ግንባራቸውን እንደቋጠሩ ተናግረዋል። እንዲያውም ጋዜጠኞቹ በዜና ጭምር ማስተማር እንዳለባቸውም ማሳሰቢያ ቢጤ አክለዋል።…መቼም የአራምባና ቆቦ ዲስኩር ‘አጃኢብ’ እንጂ ሌላ ምን ይባላል?…እናንተዬ እኔ የምለው የሌለ ነገር እንዴት ነው ሊቆጠብ የሚችለው?…ምናልባት ናቅፋ ተራሮች ውስጥ ያኔ በእብሪት በተዘጋጀው የሻዕቢያ የኢኮኖሚ መመሪያ ላይ ‘ከዜሮ ላይ መቆጠብ ትርፋማ ያደርጋል’ የሚል ነገር ተፅፎ ይሆን እንዴ?–እኔ አላውቅም። ወዲ አፎም ግን ጠንቅቀው ያውቃሉ። ለዚህም ነው– ከሌለ ውሃ ላይ ህዝቡ ቢቆጥብ ውሃ በውሃ እንደሚሆን በመገናኛ ብዙሃናቸው ለማስተማር የዳዳቸው።…ማን ነበር ‘የጨነቀው እርጉዝ ያገባል’ ያለው?…መቼም አቶ አሳያስ ሊሆኑ እንደማይችሉ ተስፋ አደርጋለሁ።…

እስቲ አሁን ደግሞ ሰውዬው ስለ መጓጓዣ ስለደሰኮሩት ጉዳይ ጥቂት ልበል። አቶ ኢሳያስ ሀገራቸው ውስጥ ያሉት የየብስ መንገዶች የሌሉ ያህል የሚቆጠሩ መሆናቸውን ይናገራሉ–ምንም እንኳን ‘22 ዓመት ሙሉ ምን ሲሰሩ ነበር?’ የሚል ጥያቄ እንደሚያስነሳባቸው ባያውቀም። እርግጥም ይህ ጥያቄ ሰውዬውና ጠረኛ ቡድናቸው ህዝቡን ከሁለት አስርት ዓመታት በላይ ረስተውት በሌሎች ጉዳዩች ላይ ተጠምደው መቆየታቸውን የሚያመላክት ነው–የተሰማሩበት ጉዳይ የሀገሪቱን አንጡራ ሀብት በማፍሰስ ለኪሳራና ለተሸናፊነት ዳረጋቸው እንጂ። የእነ አቶ ኢሳያስ የኪሳራ ሽንፈትም እንዲህ የሚነበብ ነው።…

እንደሚታወቀው ሻዕቢያ በግንባር ላይ በጀግናው መከላከያ ሠራዊታችን ኃያል ክንድ አከርካሪው ተመትቶ ቅስሙ ተሰባብሯል፣ በተለያዩ ጊዜያት በሃገራችን ላይ የሸረበው የትርምስ ሴራም በመንግሥታችን በሳል አመራር እንዲሁም በህዝባችንና በፀጥታ ሃይሎች ንቁ ክትትል ከሽፏል፡፡ በዲፕሎማሲው ረገድም፣ የየመኗን “ሃኒሽ ደሴት”ን ወርሮ ወደ ዓለም አቀፉ ፍርድ ቤት ሄዶ “ወራሪ” ተብሎ ተሸንፎ ተመልሷል። “ራስ ዱሜራ” የተሰኘውን የጅቡቲን ሉዓላማዊ ግዛት በጠብ አጫሪነት ወርሮ ይዞ በቅሌት በኳታር አደራዳሪነት እንዲወጣ ተደርጓል። ከዚህ በተጨማሪም፣ የአቶ ኢሳያስ የትርምስ ቡድን በሰሜንና በደቡብ ሱዳን መካከል ያለው ግንኙነት

እንዲሻክር አፍራሽ ሚና ከመጫወቱም ባሻገር፣ በምሥራቅ ሱዳን ውስጥ "የቤጃ እንቅስቃሴ" የሚል አንጃ አደራጅቶ ከሱዳን መንግስት ጋር እንዲጋጭ ካደረገ በኋላ መልሶ በአስታራቂነት እየቀረበ ለሱዳን መንግሥት ባለውለታ ለመሆን ጥሯል–ውጤት ባያገኝበትም። በዳርፋር ቀውስ ውስጥ የተለመደውን "እሳት የማቀጣጠል" ስትራቴጂን ተከትሎ ተራውጦ ጠብ የሚል ነገር አለማግኘቱም ጭምር፡፡

ይህ ብቻ አይደለም። ከሶማሊያው አሸባሪ አል-ሸባብ ጋር ዛሬም ድረስ በማበር በየወሩ 80 ሺህ ዶላር ቢሰጥም፣ ተረጂው የሽብር ቡድን ግን በአሁኑ ወቅት በአፍሪካ ህብረትና በሶማሊያ ፌዴራላዊ መንግስት ሰራዊቶች በደረሰበት ጥቃት ከተደራጀ ሃይልነት ወደ ጎሬላ ተዋጊነት አሽቆልቁሎ በአንድ ቦታ ላይ ብቻ እንዲከትም ተደርጓል። በጎሳ ምክንያት በመሰነጣጠቁም እየተፈረካከሰ ነው። እናም በጥቅሉ የአስመራው የትርምስ ቡድን በየፈርጁ የሸንፈት ጽዋን ሳያቅማማ ተጎንጭቷል። ታዲያ ከዚህ ሽንፈቱ በስተጀርባ ከሀገሪቱ ህዝብ ካዝና የተወሰዱ በርካታ ዶላሮች መረጨታቸውን ልብ ይሏል። በዚህ ምክንያትም የአስመራው ቡድን እንኳንስ ጥርጊያ መንገዶችን ሊሰራ ቀርቶ የህዝቡን የዕለት ጉርስ መሸፈን አለመቻል ደረጃ ደርሷል።

ይሁን እንጂ አቶ ኢሳያስ እስካሁን በሚከተሉት የጦርነት ኢኮኖሚ ፍልስፍና ምክንያት ለተከሰተው ሀገራዊ ምስቅልቅል ህዝቡን ይቅርታ ከመጠየቅ ይልቅ፤ መንገዶች በሁለት ይከፈላሉ በማለት ድሮ የአንደኛ ክፍል የህብረተሰብ አስተማሪ መሆንን ነው የመረጡት። ይህም ሰውዬው ለገዛ ህዝባቸው ያላቸውን ንቀት በግልፅ የሚያመላክት ነው። ለነገሩ አቶ ኢሳያስ የሁከትንና የሽብር ተግባርን ይተዋሉ ብሎ መጠበቅ ከውሻ ዝባድን የመሻት ያህል ይመስለኛል–ምክንያቱም ሰውዬው ከሳህል ተራራዎች ጀምሮ የተጣባቸው የጦረኝነት ተውሳክ እንዲህ በቀላሉ ፈውስ የሚገኝለት ባለመሆኑ ነው። ለዚህ አባባሌ ሩቅ በመሄድ ላደክማችሁ አልፈልግም። ምክንያቱም በቅርቡ በመንግስታቱ ድርጅት የኤርትራና የሶማሊያ ጉዳይ አጣሪ ቡድን ለመንግስታቱ ድርጅት የፀጥታው ምክር ቤት ባቀረበው ባለ 500 ገፅ ሪፖርት፤ የአቶ ኢሳያስ አስተዳደር ከሁለቱ ማዕቀቦች በኋላም ቢሆን አል-ሸባብንና ሌሎች የጦር አበጋዞችን ከመርዳት አለመቆጠቡን ይፋ ማድረጉን በአስረጅነት መጥቀስ ብቻ በቂ ስለሚሆን ነው። መቼም እዚህ ላይ "ያደቆነ ሰይጣን ሳያቀስ አይተውም" የሚለውን የተለመደ ይትብሃል አቶ ኢሳያስን ባላስታውሳቸው የሚታዘቡኝ ስለሚመስለኝ፤ ይህንኑ ብያቸው ወደ ሌላው የ"የለም" ቃለ-ምልልሳቸው ልውሰዳችሁ።

የአስመራው "ቁንጮ" (የመጨረሻውን 'ጮ' ፊደል ወደ 'ጫ' መለወጥ አይቻልም) ወደቦችንና የአውሮፕላን ማረፊያዎችን በተመለከተም፤ በሀገረ-ኤርትራ ውስጥ ውስጥ ያሉት ወደቦች አሉን ብለን የምንናገርላቸው አይደሉም ባይ ናቸው። ነገርዬው የወደብን መስፈርት አያሟሉም ለማለት ይመስለኛል ወይም ነው። ይሁንና በአሁኑ ወቅት ያሉት የምፅዋና የአሰብ ወደቦች ማደግ

እንደሚገባቸው አበክረው ተናግረዋል። አክለውም ስለ አሰብ ብዙ ይወራል፣ ይህን ግን እኔ ፖለቲካ ነው የምለው ብለዋል። ሰውዬው ከመቼ ጀምሮ ከጦረኝነት ወደ የልማት አርበኛነት እንደተቀየሩ ባላውቅም፤ ሰውዬው ያለ ሃፍረት አሰብ ወደብን ስናሳድግ ኢትዮጵያም ሆነች ጂቡቲ ከፈለጉ ሊጠቀሙበት እንደሚችሉ ገልፀዋል። በእኔ እምነት ምንም እንኳን አሁን እነዚህ ወደቦች እዚህ ግቡ የሚባሉ ባይሆኑም፤ አቶ ኢሳያስ እንዳሉት ወደቦቹ ቢያድጉ የሚጠላ ሰው ያለ አይመስለኝም። ምክንያቱም በአንድ ወቅት ኤርትራ ውስጥ ዴሞክራሲያዊና ልማታዊ መንግስት ሲፈጠር ወደቡ ለቀጣናው ሀገሮች ሊጠቅሙ ስለሚችሉ ነው። ግና እዚህ ላይ አሰብን በተመለከተ የሚባለው ነገር ተጨባጭ መሆኑን መገንዘብ ይገባል። አዎ! እኔ እስከሚገባኝ ድረስ የአሰብ ወደብ ዋነኛ ተጠቃሚ ኢትዮጵያ ነበረች። ይህ እርስ በርስ የመጠቃቀም ጉዳይ ደግሞ በአቶ ኢሳያስ ወረራ ምክንያት ተቋርጧል። እናም ዛሬ ላይ ወደቡ የግመል መፈንጫና ውሃ መጠጫ እንጂ ሰባራ ሳንቲም ለኤርትራ አያስገኝም። ታዲያ ይህን ዓለም የሚያውቀውን ሃቅ ወደ ጎን ገሸሽ አድርገው ራሳቸው አቶ ኢሳያስ የውሸት ፖለቲካ ለመጫወት ካልፈለጉ ሳያምታቱ ዕውነታውን በተናገሩ ነበር። በተጨባጭ ሀገረ-ኤርትራ ውስጥ ያለውን ዕውነታ እንጂ፤ 22 ዓመት በትዕግስት ከጠበቀ በኋላ ጥያቄ እያነሳባቸው ያለውን ህዝብ ዓይናቸውን በጨው ታጥበው ከማስጠንቀያ ጋር "ላም አለኝ በሰማይ…" ዓይነት የተስፋ ዳቦ ሊያስጎምጡት ባልቋመጡ ነበር።

ዳሩ ግን እርሳቸው እንዲህ ዓይነት ሰው አይደሉም። ሚጢጢዬ የፖለቲካ ትርፍ እስካስገኘላቸው ድረስ ከሰማይ ወተትና ማር እናዘንባለን ከማለት የሚመለሱ አይደሉም። እናም ይህ ዲስኩራቸው በአዲሱ የሐበሻ ዓመት ህዝቡን እያስፈራሩ የማስጎምጀት አዲስ ስልታቸው መሆኑ ነው። ታዲያ በእኔ እምነት አቶ ኢሳያስ ወደቦቹን የሚያሳድጉ አይመስለኝም። ለምን ቢባል ከእስካሁኑ ልምዳቸውና ከተፈጥሮአዊ ባህሪያቸው እንዳየነው እርሳቸው የሚያሳድጉት ሽብርንና አሸባሪዎችን በመሆኑ ነው። ለዚህም ነው በርካታ ሰላም ወዳድ ወገኖች "የሽብር አባት" እያሉ የሚጠሯቸው። ያም ሆነ ይህ ግን እኔን ድማሚ ውስጥ የከተተኝ ሰውዬው ወደፊት ወደቦቹ ሲያድጉ ከፈለጉ ኢትዮጵያና ጂቡቲ ሊጠቀሙ እንደሚችሉ በአስቂኝ ሁኔታ መናገራቸው ነው። እንግዲህ ይታያችሁ!…ልማታዊው አቶ ኢሳያስ ለቀጣናው ሀገራት ሲያስቡ–"ወግ ነው ሲዳሩ ማልቀስ" አሉ ጎረቤታችን እማማ መቅደስ። እኔ እስከሚገባኝ ድረስ አቶ ኢሳያስ ሌት ተቀን ያለ መታከት እየሰሩ ያሉት ቀጣናውን በጥይትና በአዳፍኔ አረሮች ለማስጀንጀን እንጂ በልማት ለማስተሳሰር አይደለም። ይህ ደግሞ እኔ ሳልሆን መላው ዓለም የመሰከረባቸው የማንነታቸው መገለጫ ነው።

ታዲያ ቃለ-ምልልስ የሰጡት የትኛው ኢሳያስ ናቸው እንበል?…እውነተኛው የአሸባሪዎች አጋፋሪው አቶ ኢሳያስ ወይስ 'የቀበሮ ባህታዊ' ሆነው ልማታዊ ነኝ የሚሉት ኮሜድያኑ ሰውዬ?…እርግጥ ኤርትራ ውስጥ ሰውዬው ራሳቸውን ካላባዙ በስተቀር በአንድ አምሳል የሚንቀሳቀሱ ሁለት ኢሳያሶች ያሉ አይመስለኝም። በዚያች ትንሽ ሀገር ውስጥ ያሉት ሰውዬ፤ ዕድሜ

ቢጫጫናቸውም ከዕድሜ ምንም ያልተማሩት፣ ሰላምን እንደ ተላጠ የኤሌክትሪክ ሽቦ ከሩቁ የሚሸሹት፣ የሀገራቸውን ልማት 'ከድንበር ማካለሉ በኋላ ቀስ ብሎ ይደርሳል' የሚሉት፣ ኤርትራ ውስጥ ህዝቡን እያስራቡ እርሳቸው ተንደላቅቀው የሚኖሩት ብሎም አስመራ ውስጥ የምስራቅ አፍሪካን አሸባሪዎችንና ፀረ-ሰላም ኃይሎችን አቅፈው የያዙት እኛ የምናውቃቸው እውነተኛው ኢሳያስ ናቸው። እናም ስለ ልማት የሚያወሩት ሰውዬ ህዝባቸውን ለማምታታት በገፀ-ባህሪነት ያቀረቧቸው መሆናቸውን ውድ አንባቢዎቼ እንደምትገነዘቡልኝ ተስፋ አደርጋለሁ። ምክንያቱም ይኸኛው ኢሳያስ በገሃዱ ዓለም ውስጥ የሌሉ የልብ-ወለድ ዓለም ሰው በመሆናቸው ነው።

ለማንኛውም ፅሑፌን ከመቋጨቴ በፊት 'አቶ ኢሳያስ በዚህ ወቅት ይህን ቃለ-ምልልስ ለምን መስጠት ፈለጉ?' የሚል ጥያቄን ማንሳት የሚያስፈልግ ይመስለኛል። ምክንያቱም የነገሩ እምብርት ይኸው በመሆኑ ነው። እርግጥም ሰወዬው የዘየዱ ይመስለኛል። በአሁኑ ወቅት የኤርትራ ህዝብ የሚላስ የሚቀመስ ነገርን "የለም" እየተባለ በችግር ውስጥ በመሆኑ የመጨረሻው የምሬት ደረጃ ላይ ደርሷል። ይህ ወንድም ህዝብ አቶ ኢሳያስና ከስያሜው ጋር የማይተዋወቀው 'ህግደፍ' (ህዝባዊ ግንባር ለፍትህና ለዴሞክራሲ) ጫንቃው ላይ በኃይል ከተንፈራጠጡበት ወዲህ፤ የኑሮ ደረጃው ልክ ከተራራ ላይ ቁልቁል እንደተለቀቀ በርሜል ዓይነት የኋሊት ሽምጥ ጋልቧል—የሚበላና የሚጠጣ ነገር እስኪጠፋ ድረስ።…እናም ህዝቡ እያጉረመረመ ነው። የሚፈልገው የማይጨበጥና የማይዳሰስ የወሬ ክምር ሳይሆን ተግባራዊ የልማት ውጤት ነው። ዛሬን በልቶ ማደር ነው። የሻዕቢያ ጉዳይ አንገሽግሾታል። ታዲያ ይህን የህዝቡን ብሶት የተገነዘበውና ገንፍሎ ሌላ ችግር ከመፈጠሩ በፊት ሰውዬው እንደ ማንኛውም አምባገነን የ'የለምና የአብቃቅተህ ተጠቀም' ቃለ-መጠይቅን እንደ መፍትሔ ለመውሰድ ተገድደዋል። ግና ኑሮ እንደ እሬት የመረረውና ዳቦ እንኳን ሳይቀር ከሻዕቢያ ሱቆች በወረፋ ተሰልፎ የሚገዛን ይህን ህዝብ "ነገ አሳድግሃለሁ" እያሉ በማሾፍ ብሶቱን ማዳፈን ይቻል ይሆን?…እኔ በበኩሌ አይመስለኝም። እርግጥ ህዝብን ለጥቂት ጊዜያት ብቻ ማታለል ይቻል ይሆናል፣ ሆኖም ምንም ሳይሰሩለት በተመሳሳይ ዜማ ያለ አንዳች ውጤት 22 ዓመት ሙሉ በተንጠለጠለ የተስፋ ዳቦ ሊሞኝ አይችልም—ማንኛውም ህዝብ እንደ ህዝብ አመዛዛኝና ፍትሐዊ ነውና። እናም የንቀት ዲስኩር የህዝቡ ምላሽ ምን ሊሆን እንደሚችል ጊዜና ሁኔታ አቅርበው የሚያሳዩን ይመስለኛል። አበቃሁ።